# ከጥር 17-18/1999 በተከበረው የ9ኛው የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ቀን በዓል የወጣ የአቋም መግለጫ፡፡

እኛ የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች 9ኛውን በዓላችንን "የላቀ ቁርጠኝነት ለመልካም አስተዳደርና ለአርብቶአደሩ ዘላቂ ልማት በአዲሱ የኢትዮጵያ ሚሊኒየም" በሚል መሪ መፈክር የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የተከበሩ አቶ መለስ ዜናዊ፣ የአርብቶአደር ተወካዮች፣ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ከፍተኛ አመራሮች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ የአርብቶአደሩ የልማት አጋሮች፣ አምባሳደሮችና ሌሎች ታዋቂ ግለሰቦች በተገኙበት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የስብሰባ አዳራሽ በደመቀ ሁኔታ አክብረናል፡፡

ይህ ዕለት በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች በመንግሥት ሕጋዊ ዕውቅና አግኝተን ያከበርን በመሆኑ ቀኑ በኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ዘንድ ልዩ ያደርገዋል፡፡

ለሁለት ቀናት በጉዳዮቻችን ዙሪያ ያደረግናቸውን ውይይቶችና የልምድ ልውውጥ ስናጠቃልል ከዚ የሚከተሉትን የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች በጋራ የተስማማንበትን ባለ13 ነጥብ ያቋም መግለጫ አውጥተናል፡፡

1. በ8ኛው የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ቀንና ከዚያ በፊት በተደጋጋሚ ስናነሳቸው የነበሩ በርካታ የአቅም ግንባታ፣ የመልካም አስተዳደር እንዲሁም የትምህርት፣ የጤና፣ የመጠጥ ውሃ የመስኖና የመሠረተ ልማት... ወዘተ ድጋፎች ምላሽ በማግኘታቸው ለፌዴራልና ለክል መንግሥታትና ለአርብቶአደሩ ልማት አጋር ለሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የላ ምሥጋናችንን እናቀርባለን፡፡
2. ባለፈው ዓመት በጎርፍ አደጋ የተጎዱ ወገኖቻችንን የማቋቋምና የጠፉ የልማት አውታሮች ማህበራዊ አገልግሎት ተቋሞችን መልሶ የመገንባቱ ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣
3. በአርብቶአደሩ አካባቢ በሁሉም ወገኖች በተለይም በፌዴራል መንግሥትና በአጎራባች ክልሎ የተጀመሩ አበረታች የአቅም ግንባታ፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር የልዩ ድጋፍ ሥራዎ የማስፈጸም አቅምን በሚፈጥር መልኩ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣
4. በአርብቶአደር አካባቢ ያለው የግብይት እንቅስቃሴ ከአገሪቷና ከዓለም አቀፍ ገበያ ጋር ለማስተሳሰ እየተደረገ ያለው በጎ ጅምር ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣

5. የአርብቶአደር ምርት በተለይም የእንስሳት የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶች ወቅታዊ ገበያ እንዲያገኙ የማመቻቸቱንና በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻል የተጀመሩ አበረታች የመሠረተ ልማት ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣

6. በጠረፍ አካባቢ እየተካሄደ ያለውን የእንስሳት ንግድ ሕጋዊ መልክ ለማስያዝ የተጀመረው እንቅስቃሴ አርብቶአደሩን የበለጠ ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ እንዲቃኝ፣

7. አርብቶአደሩ ያለው የእንስሳት ሀብት እንደዋስትና ተወስዶ የብድር አገልግሎት የሚያገኝበት ሁኔታ እንዲመቻች እንዲሁም የተጀመሩ የብድርና ቁጠባ ማህበራት በስፋት የማደራጀትና አርብቶአደሩን ተጠቃሚ የማድረግ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥል፣

8. የአርብቶአደሩን የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ መንግሥት እያደረገ ያለውን ጥረት በማጠናከር ከአርብቶአደሩ የኑሮ ዘይቤ ጋር የተጣጣሙና የሴቶችን ተሳትፎ የሚያጠናክሩ የትምህርት አገልግሎት ተጠናክረው እንዲቀጥል፣

9. በአርብቶአደሩ አካባቢ የተጀመሩ የመጠጥ ውኃ፣ የጤና አገልግሎትና የመስኖ ልማት ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣

10. በአርብቶአደሩ አካባቢ የሚነሱ ግጭቶችን በዘላቂነት ለመፍታትና ለመከላከል የሚያስችል የተጀመሩ ጥናቶች እንዲቀጥሉና የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና አፈታት ሥርዓት እንዲዘረጋ፣

11. የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ሥርዓቱ እየተከሰቱ ያሉትን ማለትም የድርቅ፣ የጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋዎች ከግምት እንዲያስገባ እንዲሁም የአርብቶአደሩን የአደጋ ተጋላጭነት፣ በዘላቂነት ለመቀነስና የመከላከልና የማቋቋም አቅሙን ለማጎልበት የተጀመሩ በርካታ ሥራዎች በተቀናጀ መልኩ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣

12. በአርብቶአደሩ አካባቢ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት እየተተገበሩ ያሉ የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች በተቀናጀና ሥርዓት ባለው ሁኔታ እንዲፈጸሙ ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩና

13. የሚቀጥለው 10ኛው የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ቀን እንደዛሬው ሁሉ በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ በፓስቶራሊስት ፎረም ኢትዮጵያና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአርብቶአደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንዲመቻችልን እንጠይቃለን።

ጥር 18 ቀን 1999 ዓ.ም.

አዲስ አበባ